


# ናይል

Nile 7th year; publication No.4; Feburary,2021

ናይል 7ኛ ዓመት፣ ቁጥር 4፣ የካቲት 2013 ዓ.ም


# ዝክረ አድዋ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

በሙሉጌታ ዘለቀ



እለቱን በማስመልከት ጥናታዊ ፅሁፍ ያቀረቡት የባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ ምሁራን ዶ/ር ጥጋብ በዜ፣አቶ ታምሩ ደለለኝ፣ ዶ/ር ፋንታሁን አየለ(ከግራ ወደ ቀኝ)



የባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ አድዋ አከባበር በሙሉአለም አዳራሽ

125ኛው የአድዋ ድል መታሰቢያ በዓል ለመዘከር ባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ፣ ታሪክና ቅርስ አሰተዳደር ት/ት ክፍል ከባሕርዳር ከተማ አስተዳደሩ እና ከአብክመ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ጋራ በመተባበር በ19/6/2013 ዓ.ም በተለያዩ ዝግጅቶች አክብሯል።

በዕለቱ ጠዋት በነበረው መርሀ-ግብር በሙሉዓለም አዳራሽ የውይይት መድረክ የዘጋጀ ሲሆን በርካታ ህዝብ በተገኙበት የታሪክ ምሁራን እለቱን አስመልክቶ ጥናታዊ ፁሁፎችን አቅርበው ሰፊ ውይይት ተደርጓል።

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ምሁርና ተመራማሪ የሆኑት አንጋፋው ፕሮፌሰር ሹመት ሲሻኝ 125ኛውን የአድዋ ድል በዓል አስመልክቶ “የኢትዮጵያ ተደጋጋሚ ፈተናዎችና የሕዝቦቿ ምስጢር“ በሚል ርዕስ ጥናታዊ ፁሁፍ አቅርበዋል። በተጨማሪም አድዋ እና የሴቶች ሚና በዶ/ር ዋጋው ቦጋለ፣ The Victory of Adwa and its implication (የአድዋ ድል አንድምታ) በዶ/ር ፋንታሁን አየለ እና The pedagogical and psychological foundations of Ethiopia’s historic victory በአቶ ታምሩ ደለለኝ የተዘጋጁ ጥናታዊ ፁሁፎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል።

ወደ ገፅ 3 ዞሯል

## በውስጥ ገፆች


4 “ብሔር እና የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀን”....
11 ፀሀይ ናፋቂዋ( ክፍል 2)
7 “የአድዋ ድል የአስከፈለን ዕዳ”
14 ከጀግኖች ገድል በጥቂቱ
8 Bahir Dar University in the eyes of...
10 ስለ ኮረና ቫይረስ ክትባት ምን ያህል እናውቃለን?




የአድዋ ድል አከባበር በባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ መሰብሰብያ አዳራሽ




# ናይል

በኢንፎርሜሽን እና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዘዳንት ጽ/ቤት
በውስጥ ግንኙነት እና ኮሚኒኬሽን ክፍል የሚዘጋጅ ወርሀዊ ጋዜጣ

**ዋና አዘጋጅ**

ትዕግስት መኮንን

**ግራፊክስ ዲዛይነር**

ትዕግስት መኮንን

**ዘጋቢዎች**

ሙሉጎጃም አንዱዓለም
ወንዳለ ድረስ
ሙሉጌታ ዘለቀ

ትዕግስት ዳዊት

**ፎቶግራፈሮች**

ታምራት አታላይ
በሪሁን ታረቀኝ
ቤተልሄም ወርቅነህ

**አምደኞች**

በላይ መኰንን (ሊቀ ኅሩያን)
መንግሥቱ እባበይ
ሰው መሆን አላዛር

**አርታኢ**

አቶ ሀሰን ኡስማን

**መልእክተኛ**

መልሸው አጥናፉ
የመረጃ ዴስክ ባለሙያዎች

**ፀሀፊ**

መልሰው አደመ
አበባ ካሳው

**ሾፌር**

ላመስግን ጫኔ

**አባይ ማተሚያ ቤት ታተመ**
**የካቲት 2013 ዓ.ም**

Contact us:-

https://www.bdu.edu.et

http://www.twitter.com/bdueduet

https://www.facebook.com/bduethiopia

http://www.linkedin.com/school/bahir-dar-university

+251583209653

# ርዕሰ-አንቀጽ

## የአድዋ ድል ለሃገር እና ለብሄረ-መንግስት ግንባታ

የአድዋ ድል ለሃገር ግንባታ እና ለብሄረ-መንግስት ግንባታ መሰረት ነው


የዘመናዊ ሀገረ-መንግስት ግንባታ ምሥረታ (State building) የጀመረው በአውሮፓ በ1648(እ.እ.አ) ጀምሮ እንደሆነ ይታወቃል። የዘመናዊ ሀገረ-መንግስት ከጥንታዊ ግዛቶች ልዩ የሚያደርጋቸው መገለጫ ባህሪያት መካከል ነፃነት እና ልዕዋላዊነት የተቀናጀ መንግስት መፈጠር(Sovereignity)፣ የሀገራት መንግስታት ከሌሎች ሀገራት በእኩልነት ላይ የተመስረተ መስተጋብር ለማድረግ የሚያስችል አለም አቀፍ ዕውቅና መጎናፀፍ(Recognition)፣ እና ሀገራት በመካከላቸው በካርታ እና በወረቀት(ከተቻለ ደግሞ መሬት ላይ የተቀመጠ ምልክት) የተለየ ደንበሮች እና ወሰኖች (boundary)የሚሉት ይጠቀሳሉ።

ሃገራችን ኢትዮጵያ የዘመናዊ ሀገር ግንባታ ቅርፅ የያዘችዉ ከአድዋ ድል በኋላ ነዉ። የአድዋ ድል የቀኝ ገዢዎች በ 1884(እ.እ.አ) ጀርመን ሀገር በርሊን ከተማ የተስማማቡትን የአፍሪካ ቅርጫ ፕሮጀከች በመገዳደር ኢትዮጵያ ሃገራችንን ህልውና በማረጋገጥ የአውሮፓ ሀገራት ኢትዮጵያን መንግስት እውቅና እንዲሰጡ ከማስገደዱም በላይ የሀገሪቱን ወሰኖች በስምምነት እንዲቋጭ አስችሏል።

ከዚህም በላይ ዓድዋ ለብሄረ መንግስት ግንባታ(Nation Building) የራሱን ትልቅ አሻራ ጥሎ ያለፈ ትልቅ ታሪካዊ ክስተትም ነበር። የብሄረ መንግስት ግንባታ በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ የሚያመልክተው በዋናነት በዜጎች መካከል የሚፈጠር አብሮነት፣ የአንድ ሃገር ልጅነት እና ቤሄራዊ ስሜት ነዉ።

ከዚህ አንፃር የአድዋ ጦርነት ኢትዮጵያዊነት የተፈተነበት ቢሆንም ድሉ ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያዊነታቸውን በደማቸው በደማቅ ቀለም በመጻፍ ፈተናውን አልፈውታል። የዓድዋ ድል ታላቅ ብሄራዊ ስሜት የፈጠረና በኢትዮጵያውያን መካከል የአንድ ሃገር ልጅነት ስሜት እና ወንድማማችነትን አዳብሮ አልፏል።

አሁን ላይ ሃገራችን የገጠማትን የልዩነት ፓለቲካ አዙሪት ለማከም የዓድዋ ድል ስሜት ተኪ የማይገኝነት ፈዋሽ መድሃኒት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል። ስለሆነም ባዓሉን በየዓመቱ ከመዘከር ባሻገር ድሉና ቱርፋቶችን ዛሬም ሆነ ወደፊትም ለብሄረ መንግስት ግንባታችን እርሾ ሆኖ ልንጠቀምበት ይገባል።




## ዝክረ አድዋ በባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ ከገፅ 1 የቀጠለ

በፓናል ውይይቱ ላይ የተገኙት ወ/ሮ ብዙነሽ መሰረት የኢፌዲሪ ባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሚንስትር ድኤታ፣ ዶ/ር ሙሉቀን አዳነ፣ የአብከመ ባ/ቱ/ቢሮ ኃላፊ፣ አቶ አብርሃም አለኸኝ በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የርዕሰ መስተዳድሩ የሕዝብ ተሳትፎና አደረጃጀት አማካሪ እና የክልል የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ዋና ዳይሬክተር አቶ ግዛቸው ሙሉነህን ጨምሮ ሌሎች የስራ ኃላፊዎች በዓሉን አስመልክቶ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

በዕለቱ ከሰዓት በነበረው መርሀ-ግብር የአድዋ ድልን 125ኛ ዓመት በማሰብ ‘ዝክረ አድዋ የኪነ-ጥበብ ምሽት’ ተካሂዷል፡፡

በኪነ-ጥበብ ምሽቱ ዝግጅት ላይ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን ወክለው የተገኙት በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ፅ/ቤት የውስጥ ግንኙነት ዳይሬክተር ዶ/ር ታደሰ አክሎግ የአድዋ ድል የመታሰቢያ በዓል በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲከበር መቆየቱን ጠቅሰው ባለፉት 27 ዓመት በሀገር አቀፍም ሆነ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በዓሉ ትኩረት ተነፍጎት መቆየቱን አውስተዋል፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ እንደዘመኑ የአውሮፓ ሉአላዊ ሀገራት ሁሉ ራሷን የቻለች ነፃ ሀገር ሁና እንድትቀጥል የአድዋ ድል አለማቀፋዊ እውቅና እንዲያገኝ መሰረት መጣሉን ተናግረዋል፡፡

ዶ/ር ታደሰ አክለውም በመላው አፍረካ የሚገኙ ሀገራት የቅኝ ግዛት ሰለባ በመሆናቸው የተነሳ የሞራልና የስነልቦና ስብራት እንዲሁም የባሕል መፋለስ የገጠማቸው መሆኑን ጠቅሰው የአድዋ የድል በዓል “ለካስ ነጭ በጥቁር ይሸነፋል“ በሚል የይቻላል መንፈስን የፈጠረ እና ለመላው የጥቁር ህዝቦች ፋና ወጊ የድል በዓል መሆኑን ተናግረዋል፡፡

## 125ኛው የዓድዋ ድል በዓል በዩኒቨርሲቲው ባህል ማዕከል

የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ባህል ማዕከል 125ኛውን የዓድዋ ድል በዓል በዩኒቨርሲቲው የመሰብሰቢያ አዳራሽ የዩኒቨርሲቲውን ፕሮዘዳንት ጨምሮ ሌሎች ሀላፊዎች፣ መምህራን እና ተማሪዎች በተገኙበት ተከብሮ ውሏል፡፡

የባህል ማዕከሉ ኃላፊ ዶ/ር አስቴር ሙሉ ለታዳሚዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት አስተላልፈው የአድዋ ድል ለመላው የጥቁር ህዝብ መለያ ምልክት ስለሆነ በየዓመቱ በዓሉን ማክበር ብቻ ሳይሆን በወቅቱ የነበሩት ጀግኖች ደማቸውን አፍሰው አጥንታቸውን ከስክሰው አገራችንን ከቅኝ ግዛት ጠብቀው ስላቆዩን እኛ ምን እናድርግ ብለን እራሳችንን መጠየቅ እንደሚገባን ተናግረዋል፡፡

መርሃ ግብሩን በንግግር የከፈቱት ዶ/ር ፍሬው ፕሮግራሙን ላዘጋጁት አካላት ምስጋና አቅርበው በዓሉ ከዛሬ ይልቅ ነገን እንድናይ ያደረገን በመሆኑ ነጭ፣ጥቁር፣ሴት፣ወንድ ያልተለየበት የሁሉም ድል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ፕሬዘዳንቱ አክለውም አገራችን የወደፊት ተስፋ ሊኖራት የሚችለው ልክ እንደ አድዋ ጀግኖች በአንድነት በመተባበር ልዩነቶችን ወደ ጎን ትቶ በእውቀትና በክህሎት ልቆ መታየት እንደሚገባና የዓድዋ ድል በትምህርት ስርዓቱ በሰፊው ይሰርፅ ዘንድ ሁሉም የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ አሳስበዋል፡፡

በመርሃ ግብሩ በዓሉን የሚዘክሩ ጥናታዊ ፅሁፎች በዩኒቨርሲቲው ሙህራን ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል በተጨማሪም ለበዓሉ ድምቀት የሰጡት ስነፅሁፍ፣ሙዚቃና ሽለላ በባለሙያዎች የተከናወኑ ሲሆን የዳቦ ቆረሳ ስነ-ስርዓትም ተካሂዷል፡

# ሠሞነኛ

ይህ አምድ ከዜናዎች በተጨማሪ ወቅታዊ ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ ሀተታዊ ፅሁፎች ይቀርብበታል



የስልጠናው ተሳታፊዎች በጥበብ ህንፃ አዳራሽ፣ ባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ

## በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የስራ አመራር ስልጠና ፕሮግራም መድረክ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

በሙሉጎጃም አንዱዓለም

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሀገሪቱ የምትፈልገውን የሰው ኀይል በብዛትና በጥራት በማፍራት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በአግባቡ ተግባራዊ የሚያደርጉ አመራሮችን ለማውጣት ከታለመው ተከታታይ ስልጠና አንዱ እንደሆነ የተጠቆመው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የስራ አመራር ስልጠና ፕሮግራም በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጥበብ ሕንፃ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ከየካቲት 4 እስከ 06/2013 መካሄዱ ይታወሳል፡፡

የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ ጨምሮ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የተውጣጡ አመራሮች የተሳተፉበት ይህ ስልጠና የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በቀጣይ 10 ዓመታት ከተለመደው አሠራር በመውጣት በክህሎትና በእውቀት የዳበሩ አመራሮችን ለማፍራት ከታለሙ ዕቅዶች አንዱ መሆኑን ተጠቁሟል፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች ባለፉት ጊዜያት የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝን ለመከላከል የበኩላቸውን አስተዋፅኦ የማበርከታቸውን ተሞክሮ በቀጣይ በሚሠራው ሥራ ልምድ የሚወሰድበት መሆኑን ተወስቷል፡፡

ስልጠናው ከተለመደው ወጣ ባለ መልኩ ከወረቀት በዘለለ ውይይት ላይ ያተኮረና በቅንጅት ስራ የዳበረ ብሎም አንዱ ተቋም ከሌላው ጋር ተናቦ የተሻለ ውጤት ለማምጣት ልምድ መለዋወጫ መድረክ እንደነበር ተገልጿል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አመራሩ አዲሱን ፍኖተ-ካርታ

ወደ ገጽ 6 ዞሯል





የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች በቀድሞው ሴኔት አዳራሽ ባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ

## "ብሔር እና የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን"

በሙሉጎጃም አንዱዓለም

ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ከኢትዮጵያ ናሽናል ሚዲያ ሳፖርት (ENMS) ጋር በመተባበር "ብሔር እና የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን (The Ethnification of Ethiopian Media)" በተሰኘ ርዕሰ ጉዳይ በዩኒቨርሲቲው የቀድሞ ሴኔት አዳራሽ የግማሽ ቀን አውደ ጥናት (Workshop) አካሄደ

መርሃ-ግብሩ በይፋ መጀመሩን ያበሰሩት የዩኒቨርሲቲው ሂዩማኒቲ ፋኩልቲ ዲን ዶ/ር ሰፋ መካ ለታዳሚዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክትና ፕሮግራሙን ላዘጋጁት አካላት ምስጋና አቅርበው አውደ ጥናቱን ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር ላዘጋጀው የጋዜጠኝነትና የስነ-ተግባቦት ት/ም ክፍልን አመስግነዋል፡፡

ስለ አውደ ጥናቱ አጠቃላይ መልዕክት በበይነ-መረብ (Video Conference) ያስተላለፉት የኢትዮጵያ አርታኢያን ማህበር ሊቀመንበር ጋዜጠኛ ፍትህአወቅ

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

## "ብሔር እና የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን"...

ከገጽ 4 የቀጠለ

የወንድወሰን ፕሮግራሙን ላዘጋጁት አካላት ምስጋና አቅርበው የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ከጊዜ ወደ ጊዜ ምንም አይነት ፍትህና ምቾት ያላገኙ መሆናቸውን እንዲሁም ለእንግልት የተጋለጡ እንደሆኑ ገልጸዋል::

በተጨማሪም የአንዱን ሃሳብ ሌላኛው በቀጥታ መቀበል ባይችል እንኳ ሃሳቡን በነፃነት ማንሸራሸር የሚቻልበት መንገድ ቢለመድና ጋዜጠኞች የህዝብ ድምጽ መሆን የሚችሉበት ሁኔታ ቢመቻች የሚል ምክረ-ሃሳባቸውን ለግሰዋል።

ጥናት አቅራቢዎች ለሙያው ቅርብና የካበተ ልምድ ያላቸው ሙህራን ሲሆኑ ዶ/ር ተሪዬ ሽዳል ኖርወይ አገር ከሚገኘው ኤን.ኤል ኤ (NLA) ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ እና ዶ/ር ሙላቱ አለማየሁ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በበይነ መረብ (Video Conference) ጥናታዊ ጽሁፍ አቅርበዋል።

በመርሃ ግብሩ በባለሙያዎች በቀረበው ጽሁፍ ዙሪያ ምልከታ የቀረበ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የሚታዩት ተግዳሮቶች ሃሳቦችን ማንሻፈፍ፣ ማንጋደድ፣ ማማለል፣ ከብሄር አጀንዳ እንዳይወጡ ማድረግና መሰል ተግዳሮቶች መስተዋላቸውን ገልፀዋል።

በተነሱት ጥያቄዎች ዙሪያም ሰፊ ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶባቸው ውይይቱ አስፈላጊና ወቅቱን ያማከለ




## ‹‹የአድዋ ድል ያስከፈለን ዕዳ››

ከገፅ 12 የቀጠለ


ሰዎች እያሳኩ ነው። ይህ ሕልም የጣሊያኖች ብቻ ሳይኾን የዚች ሀገር ታሪክና የሕዝቦቿ አልደፈር ባይነት የሚያስቆጫቸው ፈረንጆች ኹሉ ነው። እናም የአድዋ ድል ታሪክ ለኛ ለኢትዮጵያውያን ብቻ እንዳልኾነ ኹሉ የጣሊያንን ሽንፈትም ፈረንጆች የጋራ አድርገው ስለ ወሰዱት ዕዳችንን ያስከፍሉናል። ለዚህም ነው ‹በአድዋ ጦርነት ብንሸነፍ ይሻል ነበር› የምልህ›› አሉኝ።

‹‹የሶሺያሊዝም ሥርዓት ወደ ሀገራችን ሰተት ብሎ እንዲገባ ያደረጉ አሜሪካኖች ናቸው›› የሚለው ሐሳባቸው ባይዋጥልኝም የተቀበልኩት መስዬ አመሰገንኳቸው:: ውይይታችን ቢቀጥል ወድጄ ነበር። ግን ሙሽሮቹ መጡና ግቢው በዘፈን ተናጠ። እኛም ሙሽሮቹን አጅበን ወደ አዳራሽ ገባን፤ ተለያየን። ስማቸውንና አድራሻቸውን ሳልይዝ መቅረቴ አኹን ድረስ ይቆጨኛል።

አዛውንቱን የፖለቲካ ሰው እኔ እንደ ተረዳሁዋቸው የወቅቱ የአገዛዝ ሥርዓትና በሀገሪቷ እየ ተካሄደ ያለው ምስቅልቅል ወይም ኢትዮጵያ እንደ ሀገር የመቀጠሏ ኹኔታ አሳሳቢ እየ ኾነ መምጣቱ ተስፋ አስቆርጧቸው እንጂ የአድዋ ድል ለኢትዮጵያውያን ያስገኘውን ክብርና ሞገስ አጥተውት አይመስለኝም። እየ ተካሄደ ያለው የሤራ ፖለቲካ ሥጋት ውስጥ ከቷቸዋል። እንደ ኢትዮጵያ ኹሉ በዘመናት ታሪካቸው የሚታወቁት ሶርያና ሌሎችም የዐረብ ሀገራት የገቡበትን የውድቀት ጉዞ እያየና እየሰማ የማይጨነቅና የማይሠጋ ሰው ይኖራል ተብሎ አይታሰብምና::

ግን ከአምስት ዓመታት በኋላ ዛሬ ላይ ኾነን ስናየው ኢትዮጵያ የአምላክዋ ጥበቃ የማይለያት ሀገር እንደ ኾነች ተምረናል። ሊበትኑዋት ተግተው ሲሠሩ የነበሩ ሤረኞች እየ ተበተኑ ነው። ሕዝቦችዋን እርስ በርስ አባልተው፤ ሀብት ንብረትዋን ዘርፈው፤ ዝክረ ስምዋን ሊያጠፉ የተሰለፉት ምንደኞች ዝክረ ስማቸው እየጠፋ ነው። እኒያ ታላቅ አዛውንት በሕይወተ ሥጋ ካሉ ደስታቸው ወሰን እንደ ሌለው እርግጠኛ ነኝ:: በሕይወተ ሥጋ ባይኖሩ እንኳዋ መንፈሳቸው ሐሴት ታደርጋለች።

ይህ ጽሑፍ ‹‹ኢትዮጵያዊነት›› በሚል ርእስ በማዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ የሚካተት ሲኾን፤ ከኹለት ዓመት በፊት ፌስቡክ ገጼ ላይ ለጠፌው ነበር።





## በሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ... ከገፅ 4 የዞረ

(የትምህርት ስርዓት) አውቆትና ገብቶት ሊተገበረው እንደሚገባ ተ ጠ ቁ ሟ ል ፡ ፡ በ ተ ጨ ማ ሪ ም የትምህርት አግባብነትና ጥራት ለመፍጠር የመምህራን ልማት በቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው መሆኑን አውስተዋል፡፡

በመርሃ-ግብሩ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚስቴር ከፍተኛ አማካሪ የሆኑትን ፕሮፌሰር ያለው እና ሌሎች ሙህራን የከፍተኛ ትምህርት ፖሊሲ፣ ስትራቴጅክና የፕሮግራም ሰነዶች፣ የሳይንስ ፖሊሲ ስትራቴጅክና ፕሮግራም ሰነዶችና የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች የመግቢያ ፖሊሲ ቀርበው በቀረቡት ሰነዶች ዙሪያ ሰፊ የቡድን ውይይት ተካሂዶ ነጥረው በወጡት ገንቢ ሀሳቦችና ጥያቄዎች ላይ ምላሽ ተሰጥቶ ስልጠናው ወደ ከፍተኛ ትምህርት ማህበረሰብ እንዴት መድረስ እንዳለበት አቅጣጫ ተሰጥቷል፡፡

በተጨማሪም ከመድረኩ አንኳር ጉዳዮች መካከል ተዘጋጅቶ በቀረበው የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች የቅበላ ፖሊሲ ረቂቅ ሲፀድቅ ተማሪዎችን ከተለመደው ምደባ ወደ ቅበላ የሚያሸጋግር ተግባር መጀመር እንዳለበት፣እቅዶች የአንዱ ተቋም ከሌላው ጋር የሚጣጣምና የሚናበብ መሆን እንዳለበት፣ የመምህራን አቅም ግንባታ ቅድሚያ ትኩረት የሚሻ መሆኑን የሚሉት አፅንኦት ተሰጥቶባቸው ተሳታፊዎች ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ላደረገው ደማቅ አቀባበልና መስተንግዶ ላቅ ያለ ምስጋና አቅርበዋል፡፡




በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የጥበበ ግዮን ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ያለ ኦፕራሲዎን በድምፅ ሞገድ በሚሰራ መሳሪያ (' Ultrasound machine') የታገዘ የህፃናት የአንጀት መታጠፍ ህክምና ('Hydrostatic Reduction of Intussusception')

እንዲሁም
ከዚህ በፊት በጥቁር አንበሳ÷ አይደርና ቅዱስ ጳዉሎስ ሆስፒታሎች ብቻ ይሰጥ የነበረዉን የጨቅላ ህፃናት በተፈጥሮ የአፈጣጠር ችግር ምክንያት የሚከሰት የጉሮሮና የአየር ቱቦ መገናኘት (Tracheoesophageal Fistula Repair) ሕክምና በህፃናት ቀዶ ህክምና ስፔሻሊስትና ድህረ ስፔሻሊስት ሐኪሞች የጀመረ መሆኑን በደስታ ይገልፃል፡፡

# እጅ ከምን

በዚህ አምድ የዩኒቨርሲቲው ባልደረቦች እጅ ከምን ስንል አለን የምትሉት ለአንባቢ የሚበቃ ፅሁፍ ይስተናገድበታል

## ‹‹የአድዋ ድል ያስከፈለን ዕዳ›› ከአዛውንት አንደበት

በላይ መኰንን (ሊቀ ኀሩያን)

ክፉም በሉት በጎ አንድ ልማድ አለኝ፡፡ ቦታና ጊዜ ካጋጠመኝ በዕድሜ የገፉ ሰዎችን (ሽማግሌና ባልቴት) ሳገኝ ዝም ብሎ ማለፍ አይኾንልኝም፡፡ በትሕትና ቀርቤ ማናገር እወዳለሁ፡፡ በዚህ ልምድም ብዙ ተጠቅሜበታለሁ፡፡ ያለፉበትን የሕይወት ውጣ ውረድ፣ መልካምና በጎ አጋጣሚዎችን፣ የሥራ ሕይወት ልምዳቸውን፣ የአካባቢያቸውንና የሀገራችንን ታሪክ የሚነግሩኝ አዛውንቶችን በተለያዩ ቦታዎችና ጊዜያት አግኒቼ ተምሬባቸዋለሁ፡፡

በ2007 ዓ.ም አዲስ አበባ ከተማ፣ አንድ እሑድ ቀን የሠርግ ሥርዓት ላይ ተጋብዤ አዳራሹ ውስጥ ወንበር ስይዝ ከአንድ ትልቅ ሰው ጥግ የመቀመጥ ዕድል አጋጠመኝ፡፡

አዛውንቱ ደስ የሚል ቁመናና ግርማ ሞገስ ያላቸው ሽማግሌ ናቸው፡፡ ቀስ እያልኩ አዋራቸው ጀመር፡፡ በግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኀይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በዲፕሎማትነት ብዙ ሀገራት እንደ ሠሩ ነገሩኝ፡፡

የሙሽሮቹ መዘግየት የታዳሚውን እልህ ያስጨረሰ ቢኾንም፤ እኔ ግን ከታላቁ አዛውንት ጋር እንድወያይ ጊዜ ስለ ሰጠኝ እንደ መልካም ዕድል ቈጥሬዋለሁ፡፡ የመስሚያ አካላችንን የሚፈታተነው አደንቋሪው የሙዚቃ መሣሪያ ግን መደማመጥ እንዳንችል አድርጎናል፡፡ ከአዳራሹ ወጣ ብለን ብንወያይ የተሻለ እንደ ሚኾን ስነግራቸው አዛውንቱ ፈቃደኛ ኾኑ፡፡

ከአዳራሹ ጥግ አግዳሚ ወንበር ላይ ቁጭ ብለን ብዙ ነገሮችን አነሣን፤ ጣልን፡፡ የንግግራችን ርእስ ያው የሀገሪቷ ወቅታዊ ጉዳይ፣ በፖለቲካው ተስፋ የመቍረጥ ዝንባሌ ነው፡፡ ሀገራችን ስለ አለፈችባቸው በጎና ክፉ ዘመናት፣ ሀገራችን ኢትዮጵያ በየዘመናቱ በተካሄደባት የወረራ ሙከራና ተገዳ ስለ ገባችባቸው ጦርነቶች፤ በኹሉም ጦርነቶች ቀደምቶቻችን ስለ ከፈሉት መሥዋዕትነትና ድል አድራጊነታቸው፤ አኹን ሀገራችን ስለ ገባችበት ፈተናም እያነሣን ብዙ አውርተናል፡፡ በውይይታችን መሐልም አንድ ያልጠበቅሁት ሐሳብ አነሡ፡፡

የታላቁን አዛውንት ሐሳብ ቃል በቃል ባልመዘግበውም አጠቃላይ ስሜታቸውን ወስጄ እንዲህ ጽፌዋለሁ፡፡ አዛውንቱ ያነሡት ሐሳብ እንዲህ የሚል ነበር፡ :

‹‹ልጄ በአድዋ ጦርነት ብንሸነፍ ይሻለን ነበር›› ሲሉኝ የተናገሩትን ማመን አቅቶኝ ደነገጥኩ፡፡ ‹‹ምን ማለትዎ ነው ጌቶች?›› አልኩና በጥንቃቄ ጠየቅኋቸው፡፡ ‹‹ይህን ኹሉ ዕዳ የሚያስከፍለን ምክንያቱ በአድዋ ጦርነት ነጮች መሸነፋቸው፤ ጥቍር ሕዝቦች ድል አድራጊ መኾናቸው ነው›› አሉኝ ንግግራቸውን ጠበቅ አድርገው፡፡

‹‹እንዴት?›› አልኳቸው፤ ምን ማለት እንደ ፈለጉ በስሱ ቢገባኝም ታሪኩን የበለጠ እንዲያብራሩልኝ ለመቈስቈስ፡፡

‹‹ጥያቄህ ገብቶኛል፤ ጦርነቱ የተካሄደና ድሉ የተገኘ በወራሪዋ ጣሊያንና በተወራሪዋ ኢትዮጵያ መካከል ነው ብለህ አስበህ ነው፡፡ አልተሳሳትህም፤ ትክክል ነህ፡፡ ግን የአድዋ ድል ትርጕም ከዚህ በላይ አንድምታ አለው፡፡

አየህ ልጄ! ክብርና ሞገስ ለጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን፣ ለነ እምዬ ምኒልክ፣ ለነ እቴጌ ጣይቱ ብጡልና ለሌሎችም ኢትዮጵያውያን ይኹንና፤ በአድዋ ጦርነት የተሸነፉ ጣሊያኖች ብቻ ሳይኾኑ የአፍሪካን ሕዝብ ‹‹የሚናገር እንስሳ›› እያሉ በባርነት ሲያግዙት የኖሩት አልበቃቸው ብሎ የቅኝ አገዛዝ ቀንበራቸውን ከቀን ቀን እያከበዱ ሲያስጨንቁት የነበሩት ኹሉም ምዕራባውያን ናቸው፡፡ በጦርነቱ አሸንፈው ድልን



የተቀዳጁም ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይኾኑ ‹‹ነጭ አይሸነፍም›› ብለው ራሳቸውን አሳምነው የነበሩት መላ አፍሪካውያንና የአገዛዝ ቀንበሩን መሸከም ያቃታቸው ኹሉም የ3ኛው ዓለም ምዝብር ሕዝቦች ናቸው›› ሲሉ ስሜት በሚቀሰቅስ አነጋገር ሊያስረዱኝ ሞከሩ፡፡ ሐሳባቸውን የተቀበልኩት ስለ መሰላቸው ዕድል ሳይሰጡኝ ንግግራቸውን ቀጠሉ፡፡

‹‹ጣሊያኖች ከአድዋ ድል በኋላ ለአርባ ዓመታት ተደራጅተውና ዘመናዊ መሣሪያ ታጥቀው መጥተው እንደ ወርቅ በእሳት ፈተኑን፤ በዓለም የተከለከለውን የመርዝ ጋዝ ሳይቀር ተጠቅመው በአረመኔነት ጨፈጨፉን፡፡ ፈተናው ከባድ ቢኾንም ከአምስት ዓመት መራራ ትግል በኋላ አሸነፍናቸውና የውርደት ሸማ ለብሰው ወጡ፡፡

አየህ ልጄ! ፈረንጆች በጦርነት ተሸነፉ እንጂ በተንኰል አልተሸነፉም፡፡ የጦር መሣሪያ ትጥቃቸውን አስፈታናቸው እንጂ ተንኰላቸውን አላስፈታናቸውም፡፡ የጦር መሣሪያቸውን ትተው የተንኰል መሣሪያ አዘጋጁልን፤ እርስ በራሳችን እንድንባላ የተንኰል ዕቅድ ዐቅደው ለፈጻሚዎች አስረከቡዋቸው፡፡

ሌላ ሌላውን ተወው እና የሶሺያሊዝም ሥርዓት ወደ ሀገራችን ሰተት ብሎ እንዲገባና በየትኛውም የአፍሪካ ሀገር ያልተካሄደ ሥር-ነቀል ለውጥ እንዲካሄድ ያደረጉ አሜሪካኖች ናቸው›› ሲሉ የአዛውንቱ ሐሳብ ከተራው ግንዛቤዬ ጋር አልጣጣምልኝ ብሎ ስሜቴ ባነነ፡፡

‹‹እንዴት ተደርጎ ጌቶች! ሀገራችን ኢትዮጵያ የሶሻያሊዝምን ሥርዓት በመቀበሏ ከማንም በላይ የተጎዳች አሜሪካ ትመስለኛለች፡፡ የምሥራቅ አፍሪካን ወይም የቀይ ባሕርን ቁልፍ ቦታ፣ በዋናናነት ደግሞ የ‹‹ቃኘውን ወታደራዊ ቤዝ›› አጥታበታለች'ኮ›› አልኳቸው፡፡

‹‹እውነት አለህ፤ ግን በቀሉ ከዚያ በላይ ነው፡፡ አየህ ልጄ! ‹ኢትዮጵያውያኖች እንደ ሌላው የአፍሪካ ሕዝብ ለነጮች የማይበገሩ ጠንካራ እምነትና ባህል ስላላቸው ነው› ብለው ምዕራባውያን ያምናሉ፡፡

ይህን የማንነታችን መሠረት የኾነውን እምነትና ባህላችንን ከመሠረቱ ለመናድ ደግሞ ሶሺያሊዝም አስተማማኝ መሣሪያ ነው፡፡ እነሱ፣ ምዕራባውያን በቀጥታ ገብተው ይህን እንዳያደርጉ የሃይማኖት ካባ ደርበውም፤ የጦር መሣሪያ ታጥቀውም ኹለት፣ ሦስት ጊዜ ሞክረውን ዐቅማችንን አሳይተናቸዋል፡፡ በሌላም በኩል ባብዛኛው ለፖለቲካ ፍጆታ የሚጠቀሙበትና ዴሞክራሲ የሚሉት መርሐቸው ማለቴም የአንድን ሀገር እምነትና ባህል፣ አስተሳሰብና ወኔ በእጃዙር ካልኾነ

ወደ ገፅ 12 ዞሯል

# ባህረ_ሃሳብ

ይህ አምድ የተለያዩ የሀሳብ ልዩነቶችን የሚያንፀባርቁ ዕሁፎች፣ ትዝብቶች እና ክርክሮች ይቀርብበታል

# BAHIR DAR UNIVERSITY IN THE EYES OF INTERNATIONAL STUDENTS

*By Migbaru Taddese*
*MA student , Media and Communication department*

Nile tries to explore international students' perspectives about Bahir Dar University in general and Bahir Dar institute of Technology (BiT) in particular for this month edition.

**Nile:-** Hello! I would like to ask you about your gut feeling about Bahir Dar University.

**Abdirahman:-**Thank you very much for having me. I am Abdirahman Yasin Hassan, one of the Somali students who has got the chance to study at Bahir Dar University Poly campus. I am studying Hydraulic and Water Resource Engineer. I would like to thank also the University, the management, and the government of Ethiopia for facilitating this kind of education. I am happy with the teaching-learning process. We learn in both theoretical and practical modalities. I also would like to appreciate all the facilities; our needs, like staying in the country, our residences, getting our food inside the campus, also the security we saw here as the major priority. We have a good relationship with other international students, teachers, and all the university community. Everyone is welcoming us and we feel like we are at home. My friends and I are very optimistic about being here at Bahir Dar University and in Bahir Dar city as well.

**Nile:** How many of you are here? Are you the only one who has joined the Department of Engineering?

**Abdirahman:** We are around 15 in the Department of Engineering. Some of our friends graduated last month. We are around 70 students in tall over the University. We are not the only international students though; there are also students from Eritrea, the Sudan, and South Sudan.

**Nile:** How do you see the staff of the University? What do you feel about Bahir Dar University in general?

**Abdirahman:** Most of the time, I can't say the staff is not cool. Many of them are very welcoming. The only barrier that we have as international students is the language. When we meet many people for the first time their reaction is different from our expectations because they get used to people in their localities who have the same language. Sometimes when we say we don't know Amharic, they get surprised, but at the end of the day we understand each other.

**Nile:** Ok, how do you express Bahir Dar University, particularly your campus BiT and the culture? What does it look like for foreigner?

**Abdirahman:** I am only a year away from my graduation which means, I have already adapted to the environment very well. But, for a student who comes here for the first time, it feels new and different. The food is different, for example. When we came here for the first time, the food we got in the café was quite different from the one we used to have in our home. Some of our friends were trying to eat Enjera, the Ethiopian traditional food.

**Nile:** Don't you have an equivalent one at home?

**Abdirahman:** Yeah…we have, but the taste and the size is somehow different. So we tried to talk to the Café management in the next year, and we have the alternative kind of bread. The experience is all about the language and the food barrier. But after we finish the first semester, it is like home. Everything comes to normal; the food, the language and the environment. The only hard ones were the language and the food. Some of the students used to be shy to express their feelings to the teacher. As Somali students, we, the seniors, tried to give awareness to our friends. But I would like to kindly recommend and ask the university to aware international students about the system when they first come. Since they don't know the culture well, orientation about the education system should be given; there are international students who don't know how to calculate their Grade Point Average (GPA), for instance. This kind of barrier sometimes forces students to go back to home.

**Nile:** Have you come across a kind of cultural shock as a foreign student, not only inside the campus but also outside?

**Abdirahman:** I have been to down town many times since our campus is inside the city. When we walk here and outside we see a different kind women's dressing style. We are not accustomed to that, yet we understand that the virtue of traveling out of your country. You learn more things; diversity and you appreciate people, their lives, and the way they live. I think cultural presentations in the university are good to appreciate both local and the international diversities of culture so that we will be aware of and sensitive to the different culture

> “The second thing with regard to the information is most critical. Information are written mostly in Amharic. I myself have been here for four years. I can listen Amharic, but I can't read. That is a challenge. For example, if there is an exam tomorrow written in Amharic, I will miss it. There are a lot of times that we miss most important things due to language barrier.”

**Nile:** As an international student, how would you explain the communication styles of teachers and students?

**Abdirahman:** Mostly we talk to the teacher personally before class commences and express ourselves like 'Sir I am from here and there, I do not know Amharic very well, please try to explain only in English.'

**Nile:** Do you have Somali speaking teachers?

**Abdirahman:** No, I haven't come across that here. But mostly Bahir Dar University teachers are welcoming. I thank them so much because they mostly respond to our requests. They try to understand our feelings as much as possible.

**Nile:** How do you try to get information pertinent to your educational career?

**Abdirahman:** This could happen in one of two ways.. The first is related to the offices. For most of us, it is difficult to get the location of different offices easily. Experience teaches us; we learn this through experience. But we would highly like if there were signposts with numbers that tell us the locations. That is not common. The University has that in some places, but that is not enough. So the university should have a big board that shows directions. The second thing with regard to the information is most critical. Information are written mostly in Amharic. I myself have been here for four years. I can listen Amharic, but I can't read. That is a challenge. For example, if there is an exam tomorrow written in Amharic, I will miss it. There are a lot of times that we miss most important things due to language barrier.

**Nile:** Does the university provide you with updates on various events and situations?

**Abdirahman:** Mostly the University tries to do so. For example, last year we were able to talk to the external relations officer, and we had a meeting with them generally as international students, but unfortunately COVID 19 came, and we left. We began to have good relationships through such programs. Currently, we are working together to strengthen the relations between us and the university. And I would like to emphasize that as a university of international reputability, the use of English language, along with Amharic, should be promoted. The more bilingual, and multilingual if possible, the environment the better it will be to maintain effective communication. This is mostly important not only for students like us but also for expatriate instructors who do not know Amharic.

**Nile:** Thank you very much!

**Abdirahman:** Thank you for having me. It is a pleasure to talk to you on behalf of international students.

**We will have the view of an expatriate professor about Bahir Dar university by the next edition**

## ደቀመዛሙርት

ይህ አምድ በዋነኛነት የተማሪዎች ድምፅ እና ተማሪነትን የሚመለከቱ ፅሁፎች ይቀርብበታል

# የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች የሰላም ፎረም

በሰው መሆን አላዛር
የጋዜጠኝነት እና ተግባቦት ሁለተኛ ዓመት ተማሪ

አበው በብሂላቸው "በጥባጭ ካለ ማን ጥሩ ይጠጣል" እናዳሉት አሁን ላይ በአለማችን በርካታ የሚባሉ የሰላም ዕጦቶች ሲስተዋሉ ይታያሉ:: ብዙዎች ለሰላም ቢተጉ፣ ቢወጡና ቢወርዱ የተወሰኑት ሰላምን የሚነሱ ከሆነ በሰላም ውሎ ማደር፣በሰላም ወጥቶ መግባት ላይኖር ይችላል። ሰላም ከሌለ መስራትና ማግኘት መማርም ሆነ ማስተማር ዋጋ ያጣሉ። በዚህም ምክንያት በርካቶች ለሞት ሎሎቹም ለስደት መዳረጋቸው እሙን ነው::

በሐገራችን ኢትዮጵያም በተለይ ከቅርብ አመታት ወዲህ በሰላም እጦት ሳቢያ በርካቶች ለሞት እና ለዕንግልት ሲዳረጉ ይስተዋላል። ባለፉት ሁለት እና ሶስት አመታት ደግሞ የችግሩ አድማስ እየሰፋ መጥቷል። "ትልቁ ዳቦ ሊጥ ሆነ" እዳሉት ለሀገር ተረካቢነት የታጨት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችም ምክንያቱን ሳያውቁት አንዳቸው ባንዳቸው ላይ ድንጋይ መወርወር የቅርብ ጊዜ መገለጫቸው ሆኖ ይስተዋላል።

በነገራችን ላይ ስለ ሰላም ዋጋ ለአንባቢያን ማወራት "ለቀባሪ ማርዳት" ሊሆን ይችላል።መንግስት በሀገር አቀፍ ደረጃ ሰላምን ለማረጋገጥ የሰላም ሚኒስቴርን አቋቁሞ እየሰራ ሲሆን የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴርም በሐገሩቱ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሒደት ለማስፈን እየሰራቸው ከሚገኙ ስራዎችን መካከል የዩኒቨርስቲዎች የሰላም ፎረም አንዱ ነው።

እኛም በዚህ ወር የ"ደቀመዛሙርት" አምዳችን በዩኒቨርስቲያችን ስር ተቋቁሞ የተለያዩ ስራዎችን እየሰራ ስለሚገኘው የባህርዳር ዩኒቨርስቲ የሰላም ፎረም መረጃዎችን ልናጋራችሁ ወደናል።

የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች የሰላም ፎረም ፕሬዘዳንት እና በኢትዮጵያ የሰላም ፎረም ህብረት ዋና ፀሐፊ ተማሪ መታገስ ፀጋ እንደሚለው በባህርዳር ዩኒቨርስቲ በ2004 ዓ.ም የሰላም ክበብ በሚል



የባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ የሰላም ፎረም አባለት በስፖርት አካዳሚ ስታዲየምን በማፅዳት ላይ

ስያሜ የተቋቋመው የአሁኑ የባህርዳር ዩኒቨርስቲ የሰላም ፎረም በ2008 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ የሰላም ሚኒስቴር መቋቋሙን ተከትሎ የሰላም ፎረም የሚል ስያሜ ይዞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል:: ፎረሙ ሁሉንም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የሚያሳትፍ እንደሆነ የሚናገረው ተማሪ መታገስ ፀጋ ፎረሙ ብሔርን እና ሐይማኖትን ባማከለ መልኩ የተመረጡ አስራ ሶስት የስራ አስፈፃሚ አባላት እንዳሉት ጠቁሞ ተማሪዎች እርስ በርስ ባህላና ልምድ እንዲለዋወጡ እድል ፈጥሮላቸዋል ይላል።

የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የሰላም ፎረም አሁን ላይ ምን ስራዎችን እየሰራ ይገኛል ስንል ላነሳንላቸው ጥያቄም ተማሪ መታገስ ፎረሙ ተማሪዎችን ወደ ግቢ ሲመጡ በመቀበል እና ወደ ቤተሰቦቻቸው ሲሄዱ የተሸከርካሪ አገልግሎት እንዲመቻች በማድረግ እና በመሸኘት በማድረግ ተማሪዎችን ከዕንግልት በመጠበቅ የተለያዩ ስራዎችን እየሰራ እንደሚገኝ ገልፆ

በቅርቡም የተማሪዎች የምረቃ ስነ ስርአት የተዋበ ለማድረግ የግቢ ፅዳት ዘመቻ ማድረግ መቻሉን ነግረውናል።

ከዚህ በተጨማሪም ግቢ ውስጥ ክትትል በማድረግ የዕርቅ ኮሚቴ በማቋቋም የተማሪዎችን ችግር በቀላሉ ለመፍታት የሚያስችሉ ስራዎችን እየሰራ ሲሆን እነዚህን ስራዎች ውጤታማ ለማድረግ እና ሌሎችን ልምድ ለማግኘት ያግዝ ዘንድ ፎረሙ ከወሎ ዩኒቨርሲቲ እና ከአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረጉን ነግሮናል:: ይህ የሰላም ፎረም በዋናነት በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ስር የሚገኝ ሲሆን በUSAID /የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት እና በሰላም ሚኒስቴር አጋርነት የተለያዩ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል።

የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የሰላም ፎረም አባሎችተማሪዋለደጉ(የጋዜጠኝነትና ስነ ተግባቦት ትምህርት ክፍል ተማሪ) እና ተማሪ ሐይለ እየሱስ ምንይችል (የማኔጅምንት ትምህርት ክፍል ተማሪ) የተለያዩ ችግሮች በሚፈጠሩበት ጊዜ የተማሪዎችን የእርስ በርስ ግንኙነት በማጠናከር ችግሮች እንዳይባባሱ እና ችግሮቹን በቀላሉ ለመፍታት የተለያዩ ስራዎችን እንደሚሰሩ ገልፀው ክበቡ ከዚህ የተሻለ ስራ እንዲሰራ ከዩኒቨርሲቲው እና ለሐላፊ ተወካዬች የተለያዩ ድጋፎች ያስፈልጋሉ ብለዋል።

ከዚህ ባለፈም የፎረሙ አባላት ሰላምን ከራስ በመጀመር አርዓያ በመሆን እና ትኩረት ሰጦ በመስራት በዩኒቨርስቲው ውስጥ ያለውን ሰላም ለማስቀጠል የበኩላቸውን ድረሻ እንዲወጡ መልዕክት አስተላልፈዋል::

ሰላም በገንዘብ የማይተመን፣ ለአንድ ሀገር እድገት ቁልፍ እና ወሳኝ የሆነ፣ ለሰው ልጆችም የመኖር እና ያለመኖር ጉዳይ ነው እና ሁላችንም ሰላማችንን በመጠበቅ አንዳችን ለሌላችን የሰላም ዘብ እንሁን እንላለን።

# ጤንነት

ይህ አምድ የተለያዩ ጤና ነክ ጉዳዮችና ጤንነትን የተመለከቱ ምክረ ሃሳቦች ይቀርብበታል

## ስለ ኮረና ቫይረስ(COVID_19) ክትባት ምን ያህል እናውቃለን?

በአለም ዙሪያ በኮሮና ቫይረስ ምክንያት ለቁጥር የሚያታክቱ ሰዎችን ሞት ዜና በየቀኑ መስማት ከጀመርን አንድ አመት አለፈን:: በቫይረሱ የሚጠቁ እንዲሁም የሚሞቱ ሰዎች አሁንም እንደቀጠለ ነው::

ወረርሽኙን ለመከላከል የሚያስችል ክትባት ለማበልፀግ በዓለም ዙሪያ በርካታ የምርምር ቡድኖች ሳይንሳዊ ጥናቶችን ሲያካሂዱ ቆይተዋል፤ በማካሄድም ላይ ይገኛሉ::

**ጥቂቶቹም ውጤታማ መሆናቸው ተገልፆ በጥቅም ላይ እየዋሉ መሆናቸው ይታወቃል::** በአሁኑ ወቅት ሀብታም ሀገራት ክትባቶቹን በገፍ መግዛት ይዘዋል::

በ አ ው ሮ ፓ ና በ አ ሜ ሪ ካ የሚገኙ በርካታ ሰዎችም በቅርቡ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ፈቃድ የተሰጣቸውን ክትባቶች በመውሰድ ላይ ናቸው::

በኛ ሀገርም በአለም ጤና ድርጅት በኩል ከ ኮቫክስ ጥምረት የተገኘውን 2.2 ሚሊዩን ክትባት በቀጣይ ወር ወደ አገርቤት እንደሚገባ በተለያዩ መገናኛ ብዙሀን ተዘግቧል::

ለመሆኑ ስለክትባቱ ምን ያህል እናውቃለን? የኮቪድ 19 ክትባትን አስመልክቶ ‘What do you know about Vaccines being developed against covid -19’ በሚል ርዕስ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ባዮሎጂ ትምህርት ክፍል ባልደረባ የሆኑተ ዶ/ር እንዳልካቸው ንብረት ያቀረበውን ፅሁፍ መነሻ በማድረግ ስለክትባቱ ግንዛቤ ለማግኘት ጠይቀናቸዋል::

ክትባት ባጠቃላይ የበሽታ አምጭ ተዋስ ወደ ሰውነታችን ሲገባ መከላከል የሚያስችል አንቲ ቦዲ ነው ይላሉ:: ክትባቱን ስንከተብ ሰውነታችን የኮሮቫቫይረስ ፕሮቲኖች እንዲሰሩ መመሪያ ይሰጣቸዋል :: ከዚያ የሰውነታችን በሽታ የመከላከል ስርዓት ያልተለመዱ መሆናቸውን ይገነዘባል ከዛም ወደ ሰውነታችን እንዳይገቡ ያጠቃቸዋል ::

ከሶስት መቶ በላይ የሚሆኑ ካምፓኒዎች ወደ 6 አይነት ክትባቶችን በማማረት ላይ ይገኛሉ ያሉት ባለሙያው ዶ/ር እንዳልካቸው የክትባት አይነቶችን፣ የሚያመርቷቸውን ካናፓኒዎች፣ ተያያዥ ጉዳዩች እንደሚከተለው ውጤታማታቸውን እና ሌሎች አቅርበዋቸዋል፡-

### How some of the Covid-19 vaccines compare

| Company | Type | Doses | How effective* | Storage | Cost per dose |
|---|---|---|---|---|---|
| Oxford Uni-AstraZeneca | Viral vector (genetically modified virus) | x2 | 62-90% | Regular fridge temperature | £3 ($4) |
| Moderna | RNA (part of virus genetic code) | x2 | 95% | -20C up to 6 months | £25 ($33) |
| Pfizer-BioNTech | RNA | x2 | 95% | -70C | £15 ($20) |
| Gamaleya (Sputnik V) | Viral vector | x2 | 92% | Regular fridge temperature (in dry form) | £7.50 ($10) |

*preliminary phase three results, not yet peer-reviewed

| | | | |
|---|---|---|---|
| Oxford Uni-AstraZeneca | Viral vector (genetically modified virus) | x2 | 2 to 8°C (6 months) |
| Moderna | RNA (part of virus genetic code) | x2 | -25 to -15°C (7 months) |
| Pfizer-BioNTech | RNA | x2 | -80 to -60°C (6 months) |
| Gamaleya (Sputnik V) | Viral vector | x2 | -18.5°C (liquid form) 2 to 8°C (dry form) |
| Sinovac (CoronaVac) | Inactivated virus (weakened virus) | x2 | 2 to 8°C |
| Sinopharm | Inactivated virus (weakened virus) | x2 | 2 to 8°C |
| Novavax | Protein-based | x2 | 2 to 8°C |
| Janssen Johnson & Johnson | Viral vector | x1 | 2 to 8°C (3 months) |

Source: UK government, Reuters


BBC

የጎንዮሽ ጉዳቱ ምን እንደሚመስል ስንጠይቃቸው እንዲህ በማለት መልሰውልናል፡-

“ከሁለት እስከሶስት ቀናት የሚቆዩ ልጆቻችን ስናስከትብ የለመድናቸው ማለትም ክትባቱ ያረፈበት ቦታ ማበጥና ትንሽ ህመም ፣ ድካም፣ትኩሳት፣ ራስ ምታት እንዲሁም የ መ ገ ጣ ጠ ሚ ያ ና የጡንቻ ህመሞች ሊኖሩ ይችላሉ:: በአጠቃላይ እነዚህ አይነቶቹ የጎንዮሽ ጉዳቶች ብዙ ጉዳት አያመጡም ክትባት ጥሩ ነገር ነው:: በክትባት ከብዙ ህይወት ከሚያሳጡ በሽታዎች እንደ ፖልዮ፣ፈንጣጣ እና የመሳሰሉት ተከላክለናል ስለዚህ የኮረና ቫይረስ ክትባቶችንም ልንቀበላቸው የሚገቡ ናቸው::» ብለዋል::

በመጨረሻም ከቫይረሱ ተ ለ ዋ ጭ ነ ት ና አስቸጋሪነት የተነሳ የክትባቱ መከላከል አቅም ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ በጥናት የተረጋገጠ ነገር የለም አንዴ ተከትበናል እና ድጋሜ መች እንደሚይዘን መገመት አይቻልም ዝለዚህ ሁልጊዜም እራሳችን መጠበቅ እና በበሽታው ላለመያዝ ጥንቃቄዎችን ተግባራዊ ማድረግ ወደ ኋላ ማለት እንደለለብን አሳስበዋል::

# ኪነጥበብ እና ባህል




ከባለፈው ዕትም የቀጠለ

በባንች ታረቀኝ

እናቴን ወድጀሻለሁ እባክሽ አብረን እንኑር እያለ አንድ ሰው ይመላለስ ጀመር። እርሷም ትንሽ ቀን ደጅ ካስጠናችው በኋላ ልጅሽን እንደ ልጄ አድርጌ እንከባከባታለሁ ብሎ ቃል ስለገባላት ጥያቄውን ተቀበለችው።ይሄኛው ባሏም ታናሽ እህቴን ከወለደች በኋላ አብሮን የቆየ አንድ አመት ብቻ ነው።

በባል ያልታደለችው መከረኛዋ እናቴ ሁለት ህፃናትን ማሳደግ ግድ ሆነባት። ሁለታችንም በተለያየ መንገድ እናስቸግራታለን፤ጧት ከመኝታችን ስንነሳ የሌሊት ልብሳችንን በማውለቅ ሌላ ልብስ ታለብሰናለች፣ ታናሽ እህቴን ፖፖ ላይ አስቀምጣ ተጸዳድታ ከጨረሰች በኋላ ታጣጥባትና ቆሻሻውን ሽንት ቤት ትጨምራለች።

እኔን ደግሞ ከአልጋዬ ላይ ታቅፋ አንስታ የመቀመጫዋ ማህል ክፍት ከሆነች ወንበር ላይ ታስቀምጠኛለች፣ከወንበሯ ስር ፖፖ ታስቀምጥና ከዚያ ላይ እንድጸዳዳ ታደርጋለች፣ስጨርስ እንደ እህቴ እኔንም አጣጥባ ሙሉውን ቀን ተቀምጬ ከምውልባት ኩርሴ ላይ ታስቀምጠኛለች፤ከዚያም ቁርሳችንን ታዘጋጃለች፣ደረቅ እንጀራ ኩንትራት የያዟትም ሆነ እንዲሁ የሚገዟት ሲመጡ እኛን እየተንከባከበች ጎን ለጎን ትሸጣለች።

እንጀራዋን የምትጋግረው ከሌሊቱ አስራ አንድ ሰአት ተነስታ በሁለት ምጣድ እስከ ጧቱ አንድ ሰአት ተኩል አካባቢ ትጨርሳለች። አንዳንድ ቀን ታናሽ እህቴ በጧት ትነሳና ትረብሻታለች።በዚህ ጊዜ ያላት አማራጭ አዝሎ መጋገር ነበር።

በዚህ ሁኔታ እንዳለን መንግስት ‹‹የድሀ ደሀ›› ለተባሉት በአስር ብር መሬት ሲመራ እርሷም አብራ ተመራች።ከዚያም ባጠራቀመቻት ገንዘብ እና ዘመድ ወዳጅም ያለው በገንዘቡ የሌለው ደግሞ በጉልበቱ አግዟት ሦስት ክፍል የጭቃ ቤት ሰራች።

የክራዩን ቤት ለቀን ከአዲሱ ቤት ስንገባ ሁላችንም ደስተኞች ነበርን፡ ፡ነገር ግን ከዚህ ሰፈር አብዛኛው ሰው ለራሱ እያበሰለ የሚመገብ ስለሆነ የለመደችውን ስራ መስራት አልቻለችም።በዚህ ሁኔታ ችግር ቤታችን ውስጥ ሰተት ብሎ ገባ።

አንድ ቀን እናቴ ስራ ፍለጋ በየመስሪያ ቤቶች እየገባች ለመጠየቅ እኔንና እህቴን ለጎረቤት አደራ ብላ ወጣች፡ ፡በግልም ሆነ በመንግስት የህክምና መስጫ ቦታዎች እና ትምህርት ቤቶች እየገባች ክፍት ስራ እንዳላቸው ጠየቀች።እንዳንዶቹ ማስታወቂያ ተከታተይ ይሏታል፣አንዳንዶች ደግሞ የትምህርት ደረጃሽ ስንት ነው? በማለት ተስፋ አስቆርጠው ይሰዷታል፤እርሷ አንደሆነች ለአንዳንድ ነገር ቀበሌ እንኳ ስትፈርም በዱካዋ ነው።ከሶስት ቀን ድካም በኋላ አንድ የግል ትምህርት ቤት ኃላፊ ያለባትን ችግር በሙሉ ካዳመጣት በኋላ ታሪኳ ስላሳዘነው ምንም እንኳ ባትማር ፅዳት እንድትሰራ ቀጠራት፤እንዲሁም ታናሽ እህቴ በነጻ እንድትማር ፈቀደላት፤እናቴም ባለሀብቱን ከልቧ አመሰገነችው፣እኔ ግን ደስተኛ አልሆንኩም፣አንድ ግቢ ውስጥ ብቻዬን እንዴት እንደምውል ሳስበው ውስጤ መፍራት ጀመረ፣ብቸኝነት ተሰማኝ፣ ትታችሁኝ አትሂዱ ለማለት ደግሞ የማይታሰብ ነገር ነው።

ከዚያን ቀን ጀምሮ እናቴ ከሌሊቱ አስር ሰአት ተነስታ ምግብ ታዘጋጃለች፤ ለእርሷ እና ለእህቴ ምሳ ትቋጥራለች።ለእኔ ደግሞ በባለ ግጣም ሳህን ምግቤንና ውሃ በጆግ ከብርጭቆ ጋር አድርጋ ከኩርሲዬ አጠገብ ታስቀምጥልኛለች።አስራ ሁለት ሰአት ሲሆን ሁለታችንን ቀስቅሳ እኔን ታለባብሰኝና እህቴ እራሷ እንድትለብስ ታደርጋታለች፤ከዚያም ከአልጋው ላይ አንስታ ከተጸዳዳሁ በኋላ ከኩርሲዬ ላይ ታስቀምጠኛለች።ከእኔ ኩርሲ ፊት ለፊት ከፍ ባለጠረጴዛ የተቀመጠች አስራ ስምንት ኢንች ቴሌቪዥን አለች።አንድ የእናቴ የድሮ ጓደኛ አዲስ ስትቀይር ለእናቴ "ብሩን ቀስ እያልሽ ትከፍይኛለሽ" በማለት በቅናሽ ዋጋ የሸጠችላት፡ ቁርሳችንን ስንበላ ትከፍታትና እኔን እንዳይደብረኝ ሙሉ ቀን ስትለፈልፍ ትውላለች፣የእኔ ጓደኛ እርሷ ብቻ ናት።እናቴ የእኔ ብቻን መዋል ቢከብዳትም አማራጭ ስለሌላት ውስጧን እየከፋት ስማኝ ጎረቤቶቿን ‹‹ብቅ እያላችሁ እዩዋት›› ብላ እህቴን ይዛ ትሄዳለች፡ ፡እነርሱ ከሄዱ በኋላ የእኔ ስራ ቁጭ ብሎ ቴሌቪዥን መመልከት ነው። ዲሽ ስለሌን እንደፈለግሁ የተለያየ የመገናኛ ብዙሀን መከታተል አልችልም።አማራጭ ስላጣሁ እንጅ ቴሌቪዥን መከታተሉም ቢሆን ስልችት ብሎኛል።

ሰው ይናፍቀኛል፣ በተለይ ደግሞ የእኔ እኩያ የሚሆኑ ልጆች የሚያወሩትን ማዳመጥ ያስደስተኛል። ስለከተማው አስባለሁ፣ወጥቶ መግባት ይናፍቀኛል፣ፀሀይ ትናፍቀኛለች፣ሁሌም ቤት ውስጥ ቁጭ ብዬ አሻግሬ አያታለሁ፤ግን በፈለግሁ ጊዜ ልሞቃት አልታደልኩም። እንደ እኔ ስንቶቹ ይሆን ጓዳ ውስጥ ተደብቀው ፀሀይ እንደናፈቀቻቸው የሚያልፉ?

የሰውነቴ ክብደትም ሆነ ውፍረቴ ከቀን ቀን እየጨመረ መጣ፤ነገር ግን አጥንቴ ልፍስፍስ ያለ ነው።በዚህም ምክንያት እናቴ ብቻዋን ከአልጋዬም ሆነ ከወንበሬ ለማንሳት ያቅታት ጀመር። "ሳይደግስ አይጣላም" እንደሚባለው ለእናቴም አጋዥ እህቴ ደረሰችላት፤ተጋግዘው ለሁለት ያንቀሳቅሱኛል።ግን እስከመቼ ነው ይህ ሁኔታ የሚቀጥል? እህቴስ እስከ መቼ አብራኝ ትኖራለች? ይህን ሳስብ ውስጤ ይጨነቃል። በውፍረቴ የተነሳም ሁሌ ፒጃማ ነው የምለብስ፤በመሆኑም የእናቴ የድሮ ጓደኞችም ሆነ የመስሪያቤት ባልደረቦቿ ሊጠይቁን ሲመጡ በግላቸውም ሆነ አወጣጥተው ፒጃማ እና ብቻዬን ቁጭ ስል የምቆረጣጥመው ነገር ይዘውልኝ ይመጣሉ።

እናቴን የመስሪያ ቤቷ ሰራተኞችም ሆነ ጎረቤት ይወዷታል፤ያዝኑላታልም እናም እንዳይከፋት ይጠነቀቁላታል። እናቴ ስራዋን ስትጨርስ ቤት የመሄጃ ሰአት እስከሚደርስ ድረስ ከመስርያ ቤቱ ሳትወጣ ቁጭ ብላ የሌሎችን ሰዎች ነጠላ፣ጋቢ በብር ትቋጫለች፤ ትሰፋለች።

ታናሽ እህቴ ከትምህርት ቤት ስትመለስ እናቴን በስራ ታግዛታለች። ቅዳሜ እና እሁድ ደግሞ ሰንበት ትምህርት ቤት ትማራለች፤ከዚያ ስትመለስ ጥሩ ጥሩ ታሪኮችን ስለምትነግረኝ እስክትመለስ በጉጉት እጠብቃታለሁ፤ አንዳንድ ጊዜ ከእኔ ህይወት ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ታሪኮችን ትተርክልኛለች፤በዚያም እራሴን አጽናናለሁ።የዛሬ ሌሊቱ ተኩስ ግን ጥንካሬዬን የሚፈታተን ሆኖብኛል።



ዓድዋ
የኩሩ ትውልድ ቅርስዋ
የኢትዮጵያዊነት ምስክርዋ
ዓድዋ
......
ያንቺን ጽዋ ያንቺን አይጣል
ማስቻል ያለው አባ መቻል
በዳኘው ልብ በአባ መላው
በገበየሁ በአባ ጐራው

በአባ ነፍሶ በአባ ቃኘው
በለው ብሎ፥በለው-በለው!
......
ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን "እሳት ወይ አበባ" (ሁለተኛ ዕትም 1999 ዓ.ም (ገጽ 56-57)

# ‹‹የአድዋ ድል ያስከፈለን ዕዳ››

በስተቀር በቀጥታ ለማዳከም አይፈቅድላቸውም:: በመኾኑም ሶሻያሊዝም በራችንን በርግዶ ሲገባ ዝም ብለው ተመለከቱት:: ለውጥ ፈላጊው አዲስ ትውልድና የሌኒንን ወይም የስታሊንን የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ሶሺያሊዝም እንዲሁም የማኦን የልማታዊ ዴሞክራሲ ፍልስፍና ሲያነብ ወይም ሲያነበንብ የከረመው ወቅቱ ወጣት ምሁር አጨብጭቦ ተቀበለው::

የተካሄደው ለውጥ ‹‹ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም!›› በሚል መዝሙር ቢታጀብም ብዙም ሳይቆይ ምስቅልቅሉ ተጀመረ:: ሀገሪቷ በራስዋ ሀገረ-በቀል ዕውቀትና መደበኛ ትምህርት፣ ወደ ውጪም ልካ አስተምራ ለዐቅመ አመራር ያበቃቻቸውን ስልሳ ልሂቃኖቿን ባንድ ምሽት አጣች:: የሃይማኖት መሪዎችዋ ተገደሉ:: በነጭና ቀይ ሽብር ምክንያት የተማረውና የሠለጠነው አንድ ትውልድ እርስ በራሱ ተጠፋፋ:: ጀግናው የኢትዮጵያ መደበኛና ሚሊሺያ ሰራዊት አፍንጫውን ብሎ መለሰው እንጂ፤ የተስፋፊው የሶማሊያ መንግሥት፣ የሲያድ ባሬ ሰራዊት የበራችን አጥር ጥሶ ግቢያችንን ሊረግጥ ምንም አልቀረውም ነበር::

ለውጡ የራሱ የኾኑ በጎ ጎኖችም ነበሩት፤ ማለትም የመሬት ላራሹና የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት አዋጆች፣ እንዲሁም ለደርግ መንግሥት ከፍተኛ ዓለም-አቀፍ ዕውቅናን ያስገኘለት የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ፣ የሠራተኞች (ወዝ-አደሮች)፣ የሴቶች፣ የወጣቶችና በአጠቃላይም የሕዝቡ መነቃቃት፣ የሀገር ፍቅር ስሜትና አንድነት የመሳሰሉት ታላላቅ ሀገራዊ ዕሴቶች ተንፀባርቀውበታል::

ነገር ግን ሥርዓተ ማኅበሩ ከሌሎች ሀገራት እንዳለ ተኮርጆ የመጣና ዘመናትን ካስቈጠረው የኢትዮጵያ ሕዝብ የአኗኗር ሥርዓት፣ ባህልና ትውፊት፣ ልማድና ጨዋነት ጋር የማይመጣጠን በመኾኑ የእምነታችን፣ የባህላችን እና የሥርዓተ ማኅበራችንን መሠረት አናጋ::

ዘግይቶም ቢኾን ‹‹በሶቬት ኅብረትና በቻይና ልክ የተሰፋ የሶሽያሊዝም ካባ መደረቢ ኢትዮጵያን አያደምቃትም›› የሚል አስተሳሰብ የነበራቸው ኢትዮጵያውያን መሥዋዕት ከፈሉ:: ለጊዜው ግን ለውጥ አላመጡም::

ከለውጡ ማግሥት የሕዝቦችን አንድነት የሚያላሉ ኹኔታዎች እየተከሠቱ መጡ:: ‹‹የእገሌ ነጻ አውጪ ግንባር››፣ ‹‹የእንትን ነጻ አውጪ ድርጅት ወዘተ.›› የሚሉ ወይም በ ‹‹LF= Livration Front›› የሚጠሩ የብሔረሰብ ቡድኖች ከየአቅጣጫው ብቅ ብቅ አሉ::

ጣሊያኖች ሀገሪቷን በወረሩበት ወቅት ያዘጋጁትና ሳያሳኩት የቀረ አጀንዳ ነበራቸው:: ሕዝብን ከሕዝብ ለመከፋፈልና ለመነጠል አንዱን አጥቂ ሌላውን ተጠቂ፤ አንዱን ወራሪ ሌላውን ተወራሪ፤ አንዱን ጨቋኝ ሌላውን ተጨቋኝ፤ አድርገው በመቀስቀስና በፕሮፓጋንዳ ስብከት ሕዝቡ ሲከፋፈል የፋሽሽቱ ሙሶሊኒ መንግሥት የቅኝ ገዥነት ዙፋኑን አዲስ አበባ ላይ ሊዘረጋ ሕልም ነበረው:: ግን አልተሳካለትም::

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከምንጊዜውም በላይ አድነታቸውን አጠናክረው መውጪያ መግቢያ ነሱት፤ አስጨነቁት፤ አስጠበቡት:: እናም ሳይወድ በግዱ የሀፍረት ካባውን ተከናንቦና ወደዚህች ሀገር ላይመለስ ምሎ ወጣ::

ፈረንጆች ‹‹ከፋፍለህ ግዛ›› የሚለውን ክፉ መርሕ በሀገራችን ላይ ቀደም ብለው ተጠቅመውበታል:: እንደ ማሳያ የእንግሊዝ መንግሥት ዐፄ ቴዎድሮስ 2ኛን ለመውጋት የኢትዮጵያን ምድር ረግጦ ወደ መቅደላ ሲያቀና ደጃዝማች ካሣ ምርጫን (የኋላው ዐፄ ዮሐንስ 4ኛ) ከጎኑ አሰልፎ ተጠቅሞባቸዋል::

እንዲሁም የኢጣሊያ መንግሥት የምጽዋን ወደብ ይዞ ወደ ኢትዮጵያ የባሕር ነጋሽ ግዛት (ኤርትራ) መስፋፋትና ቁልፍ ቦታዎችን መያዝ ሲጀምር ዐፄ ዮሐንስ 4ኛን ለማዳከም ከምኒልክ ንጉሠ ሸዋ ጋር ስምምነቶችንን እየ ፈጸመ ኹለቱን መሪዎች የመነጠል ሥራ ይሠራ ነበር:: በኋላ ደግሞ

ከገፅ 7 የቀጠለ

የመከፋፈሉን ሥራ ከመሪዎች ወደ ሕዝቦች እንዲወርድ አድርጎ አንድን ሕዝብ (አማራ) ቅኝ ገዢና ጨቋኝ፤ ሌላውን ሕዝብ ተገዢና ተጨቋኝ የሚለውን ክፉ ሐሳቡን ለማሥረፅ ሞከረ:: ከለውጡ በኋላ ይህ ሐሳብ አዲስ በተፈጠሩት ግንባሮች መንፀባረቅ ጀመረ:: ከመንፀባረቅ አልፎም ማኒፌስቶ (መግለጫ) ተዘጋጅቶለት ሰነድ ኾኖ ጸደቀ::

‹‹የአማራው ሕዝብ የሌላው ብሔር ብሔረሰብ ጠላት፣ የኦርቶዶክስ እምነት የሌላው ሕዝብ መጨቆኛ መሣሪያ ናት›› በሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ የሐሰት ታሪክ ተጻፈ፤ የውሸት ትርክት እንደ ቅኔ ተዘረፈ:: የእርስ በርስ ጦርነት ተፋፋመ፤ የምርት ኀይል የኾነው ወጣት ትውልድ ወደ ጦርነት ተመመ::

በሰሜናውያኑ ክፍላተ ሀገራት የተለኮሰው የጦርነት ሰደድ እሳት አድማሱን እያሰፋ ለ17 ዓመታት አምራች ኀይል የኾነውን ወጣት ትውልድና የሀገሪቷን ሀብት ምጥጥ አድርጎ በላ:: በመጨረሻም የኤርትራ ነጻ አውጪ ግንባር፣ የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጪ ግንባር እና አጋሮቹ የደርግን ሰራዊት አሸንፈው ሀገር ሲቆጣጠሩና መንግሥት ለመኾን ሲያኮበኩቡ ሌላ አሳዛኝ ታሪክ ተደገመ::

ደርግ ገና ከጅምሩ የሀገሪቷን ልሂቃን ያለ ፍትሕ በጅምላ እንደ ጨረሰ ኹሉ፤ የትሕነግና የአጋሮቹ መንግሥትም ገና እግሩ የቤተ መንግሥት ምንጣፍ ሳይረግጥ ሀገሪቷ ከአንድ ምእት ዓመት በላይ የገነባችውን ዘመናዊ የመከላከያ ተቋም አፈረሰ፤ ለአንድነቷና ሉዓላዊነቷ ሲዋደቅ የኖረውን የሀገር ሰራዊት ‹‹የደርግ ወታደር›› ብሎ ያለ ፍትሕ ሜዳ ላይ በተነ:: ይህ እንግዲህ አንድን የሀገር ሰራዊት የመበተን ጉዳይ ብቻ ሳይኾን የሀገሪቷን አንድነትና የሕዝቦቿን አብሮነት አዳክሞ ሀገሪቷን ለመበተን የተወሰደ መሠሪ ውሳኔ ነበር::

ይህ ብቻ አይደለም የወያኔ መንግሥት በሀገሪቷ ያሉ ምሁራንን ቅስም ለመስበርና ስለ ሀገራቸው ታሪክ፣ ባህልና ስለ ሕዝቦቿ አብሮነት ቀና ብለው እንዳይናገሩ ለማድረግ የአንጋፋው የትምህርት ተቋም፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 42 መምህራንን ከሥራ አባረረ:: ይህም በሀገሪቷ የትምህርት ዕድገት ላይ የተፈጸመ ሌላው ሤራ ነበር::

በኢሕአዴግ ዕውቅና ሰጪነት ኢትዮጵያ ሰሜናዊቷን ክፍለ ግዛቷን ኤርትራን አጣች:: በ3000 ዓመታት ታሪኳ (5000 ዓመታት የሚሉ የቅርብ ጊዜ መረጃዎችም አሉ::) ኢትዮጵያ በየዘመናቱ የባብ እልመንደብ፣ የአዱሊስ፣ የዘይላ፣ የበርበራ፣ የምፅዋና የአሰብ ወደቦችንና የባሕር በሮችን እንደ ፈለገች ተጠቅማ በየዘመናቱ ከተነሡ የዓለም ሥልጡን ሀገራትና መንግሥታት ጋር በታሪክ፣ በሥልጣኔ፣ በንግድና በፖለቲካ እንዳልተፎካከረች ኹሉ በ21ኛው ምእት ዓመት የባሕር በር የሌላትና ወደብ-አልባ ሀገር ኾነች::

የዓለምን የፖለቲካ ሚዛንና የሶቬት ኅብረትን መፈራረስ ተከትሎ ለሶሽያሊዝም ሥርዓት ጀርባውን የሰጠው የኢሕዴግ መንግሥት በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ርእዮትና በብሔር-ተኮር ፌደራላዊ ሥርዓት መንግሥቱን አዋቀረ:: ቋንቋንና የዘውግ ፖለቲካን መሠረት አድርጎ የተመሠረተው ፌዴራላዊ የመንግሥት አወቃቀር ነባሩን የሕዝቦች አብሮነት እያላላ ሲመጣ የጠባብነት ዘር በምድሪቷ ተዘራ::


ገና ከማለዳው ‹‹ከክልሌ ውጣልኝ ማለት ተጀመረ፤ የጥላቻ ፖለቲካን በፀነሱ ካድሬዎችና ታጣቂዎች ክብሪት ተቀጣጠለ፤ ምስኪኑ ዜጋ በተለይም የአማራ ሕዝብ ሀገሬ ከሚላት የኢትዮጵያ ምድር፣ ተወልዶ ካደገበትና ከኖረበት ቀዬ ወጥቶ ወደማያውቀው የቅድመ አያቶቹ ሰፈር ሂድ ተባለ፤ በመሣሪያ ኀይል ተፈናቀለ፤ ተገደለ፤ ይሄው አሁንም አለ፤ እየ ቀጠለ፣ እየ ቀጠለ…››

ጣሊያኖች ራሳቸው ያላሳኩትን ሕልማቸውን በራሳችን

# የሳይንስ ጥግ

ይህ አምድ ሳይንስ እና ቴክኖሎጅ ነክ የሆኑ ፅሁፎች ይቀርብበታል

**PALM CITY- Bahir Dar is an Android mobile application developed by the collaboration of Geospatial Data & Technology Center (GDTC) and Research and Community Services Vice President Office of Bahir Dar University.**






**PALM CITY-Bahir Dar tourist mobile application is freely available in Play Store and anyone can down load it by writing the name on the search window of Play Store without restriction. The setup file has 5.9MB size and can work in all android devices. The installation process is simple and similar to other mobile applications.**

**PALM CITY-Bahir Dar**

*PALM CITY-Bahir Dar is an Android mobile application intended to help tourists and people new to Bahir Dar city. PALM CITY-Bahir Dar is developed by the collaboration of Geospatial Data & Technology Center (GDTC) and Research and Community Services Vice President Office of Bahir Dar University.*

**Support**

*Unlimited text*
*Image*
*Video and*
*Audio formats*

**Function**

*Current location finder*
*Heaps of business details*
*Route planning*
*Offline & online searching*
*Nearby search*

**Uniqueness**


*Accurate Data & map accuracy*
*Data access control*
*Level of datelines*
*Made in Bahir Dar university*

# ስብጥር

ይህ አምድ በሌሎች አምዶች ያልተስተናገዱ ልዩ ልዩ ፅሁፎች ይቀርብበታል

## ከ ጀግኖቻችን ገድል በጥቂቱ

በመንግሥቱ እባበይ




በአድዋው ጦርነት የሞቱት የኢትዮጵያ ጀግና ወታደሮች ስም ዝርዝር አሁንም ድረስ በውል አይታወቅም፡፡ እነሱ ሀገራቸውን በክብር ለትውልዳቸው ቢያስተላልፉም ስማቸውን ግን በትክክል ጽፎ የሚያስተላልፍላቸው አልተገኘም፡፡ እንደምን ያለ ገድልና ታምር እነማን እንደሰሩ በቂ ታሪክ አልተመዘገበም፡፡ እንኳንስ የተራው ሰራዊት ይቅርና የጦር አለቆቹም ስም በሚገባው ልክ አልተጻፈም፡፡ይሁንና በአንዳንድ መጸሀፍት እጅግ ጥቂቶቹ ብቻ ተጠቅሰው እናገኛቸዋለን::

የትልልቆቹን መኳንቶች ስም በጥቂቱ እንደሚከለው ይታወሳል፡፡

- ታላቁ የመኮነን አርበኛ የንጉሰ ነገስቱ የአክስት ልጅ ደጅ አዝማች በሻ፣

የፈረሱ መሪ ተብሎ ስሙ በእውነት የተጠራው፤ አፄ ሚኒሊክ ሸዋ በገቡ ጊዜ የአፄ ዮኒንስ ሰራዊት በሜዳ መርቶ ሲጎዝ አይቶ “በማን አገር ሜዳ እንዲህ ሆነህ ትጓዛለህ?” በማለት በፈረስ ዘልቆ ባለ ቀሚሱን የጣለውና “50 ሰንአዲር ዋስ የጠራችሁ በሻሃ አቦየ ከፈለሳችሁ” ተብሎ የተዘፈነለት አርበኛ ነው፡፡ እርሱ ግን ካልጋ ወርዶ ከበቅሎ ላይ፣ ከበቅሎ ወርዶ ከፈረስ በመሆን ተቀማጥሎ ያደገው ባለ መጣምር ፈረሱን ሁለት ሁለት ቃዳ መሬት የሚራመደውን ልጓም ይዞበት በአንድ ወገን በእግሩ ሲሮጥ ከአባራሪ እጅ ወደቀ፡፡

- ሌላው ጀግና ፊት አውራራ አባ ውርጅ ይባላሉ፡፡

በሀረር የራስ መኮነን ጭፍራ ናቸው፡፡ በአላጌው ጦርነት ማዦር ቶዘሊ ለመሸሽ መንገድ ጀምሮ ሳለ ከፊት አውራሪ አባ ውርጅ ጋር ተገናኘ፡፡ ቶዘሊ ሽጉጡን እስኪያወጣ ድረስ አባ ውርጅ ጊዜ አልሰጠውም ነበር:: እንደነብሩ ግልገል ተወርውሮ ተከመረበት እና ትግል ገጠሙ፡፡ በዚያው ተያይዘው ገደል ገቡ እና የሁለቱም ፍጻሜ አንድ ላይ ሆነ፡፡ “ጀነራል ባህር ማጀርቶ ቶዞሊ ማን ይነካዋል ያለ ፈጣሪ ገደል ሰደደው አንድ ፊት አውራሪ” ተብሎ በግዜው ተገጥሞለታል፡፡

- ሌላው አርበኛ ጎላን

የተሾመው ደጅ አዝማች ጫጫ መሀል ለመሀል ዘልቆ በመታገል ጣሊያኖችን መድፍ አስለቅቆ በዚያ ላይ ወደቀ፡፡

- ጊዳን ገብሬ፡፡

ጊዳን ገብሬ በአላጌው ጦርነት ከወደቁት ጀግኖች መካከል አንደኛው ናቸው፡፡ የላስታ እና የዋግ ጦር መሪም ነበሩ፡፡ በገደል እየተቆናጠጡ፤ የተታኮሱ ጥይታቸውን ጨርሰው ጠላትን በጎራዴ ሲከተክቱ አምባላጌ ላይ ወደቁ፡፡
ከዚያ ወፍጮ ቢወቅሩት አይለሰልስም በጊደን መንደር ማንም አይደፍርም” ተብሎ ተገጠመላቸው ፡፡

- ሌላው ጀግና ፊት አውራሪ ገበየሁ ነበሩ፡፡

አርበኛው ፊት አውራሪ ገበየሁ የግራው በሬ የአምባላጌን አምባ ጋሻ እና ጠመንጃ ሳይዝ ዘንግ ይዞ የሰበረው በዚያም ቀን እንዲህ ተብሎ ተገጠመለት፡፡ “ኢጣሊያ መቶ ታቦት የሚያረክሰው ገበየሁ በሞቴ ግባና ቀድሰው፡፡” እንዲህ የተዘፈነለት ጀግና የንጉሱ ፊት አውራሪ በዚሁ ጦርነት መስዋእት ከሆኑት አንዱ ነው፡፡

ሌላኛው ጀግና ስሙ አልተመዘገበልንም፡፡ በተግባሩ ግን ኢጣሊያኖች ሳይቀሩ መስክረውለ ታል፡፡ መቀሌ ላይ የነበረውን የጠርሙስና የእንጨት ስባሪ አልፎ የብረት ሽቦ ጥሶ በሰውነቱ ደም እየተዘራ ምሽጉን ሊያፈርስ አስቦ መቆፈር ሲጀምር በጥይት ተመቶ ወድቋል፡፡

- ፊት አውራሪ ተክሌም

ንጉሰ ነገስቱ ለልጃቸው ሞግዚት አድርገው ወለጋ ላይ የሾሙት እንደዚሁ ወደቀ፡፡

- ቀኛ አዝማች በሻሀ እና ጸሀፌ ገብረ ጻድቅ ወልደ ሀዋርያት

ከመቀሌዎቹ ጀግኖች መካከል ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህ የሀረር ወታደሮች የመቀሌን ምሽግ አጥሩን ጥሰው መሰላል ዘርግተው ወደ ውስጥ ለመግባት ሲሞክሩ እምሽጉ ላይ ወድቀው የተሰው ጀግኖች ናቸው፡፡

ያ አድጎ ያልጨረሰው ቀኛ አዝማች ታፈሰ እንኳን ሰውና ያውድማው ዝሆን ሲፎክር ድምጹን ሲሰማ ይጨነቅ ነበር፡፡ ሲተኩስም፣ ፈንጅ ሲጥል፣ በጎራዴ ሲመታ ከሁለተኛው ሰልፍ ሰማእት ከሚባለው አገር ሲደርስ ክንዱ ቆሰለ፡፡በቆሰለም ጊዜ አሽከሮቹ “እንግዲህ ከጥላ እናሳርፍህ” አሉት፡፡ እርሱ ግን “ለጣሊያን ወታደር አንድ እጄ ይበቃዋል” ብሎ ጠላት ሲያባርር ከዚያ ላይ ወደቀ፡፡

ወየው ወየው እኔስ ለፈረሱ እና ለጠመንጃው አለቅሳለሁ ያውድማ ዝሆን አይቆምለትም ያልነው የዋዛ አልነበረም፡፡ በሚገዛው አገር የዝሆን ማደኛ ነበረው፡፡ እሱም ከንጉሰ ነገስቱ መግደያ ነፍጥ ይሰጠኝ ብሎ ለመነ፡፡

ሚኒሊክም በአንድ ጊዜ ተኩሶ የሚጥለውን መሳሪያ ሰጡት፡፡ እሱም ከአሽከሮቹ ጋር ሆኖ ዝሆኑን ሲያባርር እና ሲገድል ይውል ነበር፡፡ የገደለውንም ዝሆን ቁጥር አይታወቅም ነበር፡፡ አሽከሮቹ ግን አስርም አስራ አምስትም ይገድሉ ነበር፡፡ የዝሆን ጥርሱንም ለንጉሱና ለንግስቲቱ እንደፍልጥ እያሰረ ያስገባ ነበር፡፡

የንጉሰ ነገስቱም ሰራዊቶች በወቅቱ እባክህ አጋርህ አድርገን እያሉ ወደ እርሱ ይሄዱ ነበር፡፡ ምን ያደርጋል ይህን ሁሉ ያልንለት ሰው እሱም እንደሌሎቹ ሁሉ አሁን የለም፡፡

- ሌላው ደግሞ ፊት አውራሪ ዳምጠው ናቸው፡፡

ፊት አውራሪ ዳምጠው ወደ ሞስኮው ንጉስ ተልኮ ሄዶ የነበረው ያ በንግግሩም በመልኩም ተመርጦ የነበረው እሱም እንደዚሁ ጠላት ሲያባርር ወደቀ፡፡

እነሆ በዚያን ቀን የወደቁት የኢትዮጵያ መኳንንትና ሰራዊት ደማቸውን እንደ ሰማዕቱ ጴጥሮስ ለዓለም ጥቁር ህዝብ ሁሉ ደመ-ማህተም ሆኖ ዛሬም ድረስ ይታወሳል፡፡

ቤርክሌይ የተባለው እንግሊዛዊው ጸሃፊ ስለአድዋ ጦርነት በጻፈው መጸሀፉ በኢትዮጵያዊያን በኩል በጦርነቱ የሞተውን ሰው ቁጥር 7560፣የቆሰለውን 10 ሺህ አድርጎ ጽፎታል፡፡

በኢጣሊያኖችም በኩል የሞቱት 6133፤ የተማረኩት 1865 ይሆናሉ ብሎ ጽፏል፡፡

የአድዋ ጦርነት በጀግኖች አባቶቻችን ድል አድራጊነት በዚህ መልኩ ተጠናቀቀ፡፡
ዛሬን አያድርገውና ስልጣኔ ከርሷ መንጭቷል፤ተምሳሌትነቷም ብዙ ነው፤ መታወሻዋም ነጻነት ነው፡፡
የሰው ዘር በኩር መገኛም ነች::
የአያሌ ታሪክ ባለቤት ኢትዮጵያ ሁሌም ከፍ ትበልልን!!

### ዘላለማዊ ክብር እና ሞገስ ለአድዋ ሰማዕታት!!

ምንጭ፡- የዚህ ጽሁፍ አብዛኛው መረጃ ሸገር ኤፍ ኤም 102.1 ካደመጥኩት ታሪክ የተወሰደ ነው፡፡

# እንግዳ

ይህ አምድ የዩኒቨርስቲው ሰራተኞች፣ ተማሪዎች ወይም ሌሎች ታዋቂ እና ተፅኖ ፈጣሪ ሰዎች በዕንግድነት ይቀርቡበታል

የዚህ ወር እንግዳችን በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አትክልተኛና ፅዳት ሰራተኛ የሆኑት ቄስ ሞላ መንግስት በቅርቡ በኮሌጁ ከፍተኛ አፈፃፀም አስመዝግበው ተሸላሚ ከነበሩት ትጉህ ሰራተኞች መካከል አንዱ ናቸው::

ከዝግጅት ክፍላችን ጋር አጠር ያለ ቆይታ አድርገዋል፤ቃለ-ምልልሱን እነሆ:-

**ናይል:-** በቅድሚያ ለቃለ-ምልልሱ ፈቃደኛ በመሆንዎ በዝግጅት ክፍላችን ስም እያመሰገን በቅድሚያ ስምዎትንና የስራ ድርሻዎትን ቢነግሩን?

**ቄስ ሞላ:-** ስሜ ሞላ መንግስት እባላለሁ፤የስራ ድርሻየም አትክልትና ፅዳት ሰራተኛ ነው

**ናይል:-** ስለ ቤተሰብዎ ቢያጫውቱን?

**ቄስ ሞላ:-** ትዳር መስርቸ ወልጀ ለስራ የደረሱ ልጆችንም አድርሻለሁ የሚማሩትንም በማስተማር ላይ እገኛለሁ:: ሁሉም ቤተሰብ አንዳችን ከአንዳችን በመከባበርና በመተሳሰብ እየኖርን ነው፤እኔም በተቻለኝ አቅም ለቤተሰቦች ፍቅር በመስጠጥ፣ማታ ማታ አንዳንድ ቀልዶችንና እንቆቅልሾችን እያወራን እንጫወታለን::

**ናይል:-** ወደ ዩኒቨርሲቲው መቼ ተቀላቀሉ?

**ቄስ ሞላ:-** የተቀጠርኩት በ2011 ዓ.ም ጀምሮ ነው

**ናይል:-** አትክልቶችን መንከባከብ የሚሰጠው ደስታ እና እርካታ እንዴት ይገልፁታል?

**ቄስ ሞላ:-** የተተከሉት አትክልቶች ቀን በቀን ከተንከባከቧቸው በአንድ ሌሊት ለውጥ ያሳያሉና አድሬ ስመጣ ደስታ ይሰማኛል፣ከዚያም ሌላ የተሻለ ነገር ለማየትና ምንም እንዳይሆኑ በማሰብ ቧት እና ማታ ውሃ በማጠጣት ልዩ የሆነ እንክብካቤ አደርግላቸዋለሁ፤አረም እንዳያቀረጭጫቸው በወቅቱ አርማለሁ፣እኮተኩታለሁ ሰዎች እንዳይቆርጧቸውና ቆሻሻ እንዳይጥሉባቸው እቆጣጠራለሁ::

**ናይል:-** ባህርዳር የኒቨርሲቲን እንዴት ይገልፁታል?

**ቄስ ሞላ:-** እኔ እስከማውቀው በጥሩ ሁኔታ ስራዎችን እያከናወነ ስለሆነ በዚሁ ይቀጥል እላለሁ

**ናይል:-** ተማሪዎችን በተመለከተ የሚሉት ነገር ካለ?

**ቄስ ሞላ:-** ተማሪዎች በተመደቡበት የትምህርት መስክ ጠንክረው እንዲማሩና በስነ-ምግባርም ታንፀው የትምህርት ሰዓታቸውን በማክበር በሰዓቱ እንዲገቡና እንዲወጡ እላለሁ::



ቄስ ሞላ መንግስት በጥበበ ጊዮን ሆስፒታል በስራ ላይ

**ናይል:-** በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ምስጉን ሰራተኛ ሆነው በኮሌጅ ደረጃ ተሸላሚ በመሆንዎ ምን ተሰማዎት?

**ቄስ ሞላ:-** ታላቅ ደስታ ተሰምቶኛል፤ከዚህ በበለጠ የተሰጠኝን የስራ ድርሻ በከፍተኛ ራዕይና ተልኮ ለማከናወን በር ከፍቶልኛል::

**ናይል:-** ለዚህ ሽልማት ያበቃዎት የጎላ ስራ ምን ይሆን ብለው ያስባሉ?

**ቄስ ሞላ:-** የተሰጠኝን የስራ ድርሻ በጥሩ ሁኔታ ማከናዎን መቻሌ፣ሰዓት በማክበሬ፣ በቅን በመታዘዜ፣ህዝብን በማክበሬና የተጣለብኝን ኃላፊነት በአግባቡ በመወጣቴ ነው ብዬ አምናለሁ::

**ናይል:-** የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ግቢ ከዚህ በበለጠ አምሮና ተውቦ እንዲታይ ለወደፊት ምን አቅደዋል?

**ቄስ ሞላ:-** አጠቃላይ ግቢው በኮሌጁም ሆነ በሆስፒታሉ ዙሪያ ከሰራተኛውና ከተማሪው አልፎ የበሽተኞችን ሆነ የአስታማሚዎችን መንፈስ የሚያድስ ሆኖ እንዲታይ አልሜ ሁልጊዜ አትክሎቶችን እንከባከባለሁ፤

ለዚህ ስሜቴን ይገልፅልኛል ብየ ያሰብኩትን ግጥም ልሞክር:-

እስኪ በስማም ብየ ልጀምር ድርሰት፣
በጥበበ ግዮን ምን ጥፋት አላት፣
ዙሪያው ሆስፒታሉ ተውቦ በአትክልት፣
አስታማሚው ሁሉ በጣም ቀናበት::
ኃላፊው እንደንብ ዶክተሩ ፈረንጅ፣
የፈጣሪን ስራ በእጁ አረገው እንጂ::
ለስራ እንትጋ በአንድነት ሁላችን፣
ሞት አይቀርምና ሲጠራ ፋይላችን::
በዊዝደም ዙሪያ ውስጥ ለሽለሙን አካል፣
ምን ሳድርግላቸው አቅም የለኝ ለካን::

**ናይል:-** ሌሎች ሰራተኞች በተሰማሩበት የሙያ መስክ ተግተው እንዲሰሩ ምክረ ሃሳብዎን ቢያካፍሉን?

**ቄስ ሞላ:-** ሁሉም ሰራተኛ የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጣና የስራ ሰዓት ከማክበር ጀምሮ ስራቸውን በትጋት አከናውነው ለሽልማት እንዲበቁ እላለሁ

**ናይል:-** ስራዎትን በሚፈልጉት መልኩ ለማከናዎን አስበው ያጋጠምዎት ተግዳሮት ካለ ቢገልፁልን?

**ቄስ ሞላ:-** እኔ ለአትክልቶች ልዩ ፍቅር ስላለኝ ባለው ነገር እየተንከባከብኩ ለምልመው እንዲታዩ አደርጋለሁ እንጂ ለአትክልተኛ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ማለትም ለአትክልት ማስተካከያ ማሽን፣ የውሃ ፑዝ (ረጅሙ የፕላስቲክ ትቦ)፣አካፋ፣አዷማ፣ማጭድ ወዘተ...የመሳሰሉት እና የደንብ ልብስ እንዲገዙልን በተደጋጋሚ ብንጠይቅም ሲገዙልን ባለመቻላቸው አንዳንዴ ከቤቴ የግሌን ቁሳቁስ በማምጣት እሰራለሁ::

**ናይል:-** ዩኒቨርሲቲው ማድረግ ያለበትን ነገር ቢጠቁሙን?

**ቄስ ሞላ:-** እኔ ካየሁት አንፃር ለመግለፅ ብሞክር አጠቃላይ የሆስፒታሉም ሆነ የኮሌጁ አጥር በዘመናዊ መልክ እንዲታጠር ቢደረግ፣ሌላውና ትኩረት የተነፈገው ነገር ግን ከፍተኛ ችግር ያለው ከሆስፒታሉ በስተደቡብ አቅጣጫ የሚገኘው ደልዳላ ቦታ የውሃ ማፋሰሻ ስለሌለው ውሃ አቁሮ በመያዝ ለወባ ትንኝ መራቢያና ለሌሎች ችግሮች መነሻ ስለሆነ የሚስተካከልበት መንገድ ቢመቻች::

**ናይል:-** ሌላ የሚጨምሩት ነገር ካለ?

**ቄስ ሞላ:-** እነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸው ነገሮች በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲስተካከሉና እንዲሟሉ ትኩረት ይሰጣቸው እላለሁ::

**ናይል:-** ለነበረን ጊዜ በጣም እናመሰግናለን::

ቄስ ሞላ:- እኔም አክብራችሁና መርጣችሁ እንግዳ ስላደረጋችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ::



Professor Meareg Amare Chemistry Department, Science College



Proessor Temesgen Baye History & Heritage Management Department, Social Science Faculty

*Your hard work has finally paid off and*
*Bahir Dar University admire your devotion.*
*We are happy for your promotion dear professors!*

# CONGRATULATIONS!






The first batch of PhD in Public Health candidates from College of Medicine and Health Sciences, School of Public Health.